## ለጉብኝት እንኳን ደህና መጡ

ቤተሰቦችንና ጓደኞችን ለመጠየቅ በአረጋውያን መንከባከቢያ ቤቶች ፣ በጤና እና እንክብካቤ ተቋማት ውስጥ እንኳን ደህና መጡ።

ኮሮና ለአረጋውያን እና ለታመሙ በጣም አደገኛ የሆነ ተላላፊ በሽታ ነው።

## ስለሆነም እነዚህን ምክሮች መከተል አለብን

• ሙሉ ጤናማ ካልሆኑ ለመጎብኘት አይመጡ ፣ ይልቁንስ ስልክ ይደውሉ።

• የኮሮቫይረስ የደም ምርመራ ምላሽ እየጠበቁ ከሆነ አይጎበኙ።

• ላለፉት 10 ቀናት ከኖርዌይ ውጪ የቆዩ ከሆነ አይጎበኙ።

• በቤት ውስጥ የኳራንቲን / ራስን ለይቶ መቆያ/ ገለልተኛ ከሆኑ ወይም የኮሮናቫይረስ በሽታ ካለበት። ሰው ጋር በቅርብ ተገናኝተው ከሆነ አይጎበኙ ።

## መጎብኘት ከቻሉ ይህንን ያስታውሱ

• ከመምጣትዎ በፊት ከተቋሙ ጋር ጉብኝት ማመቻቸት አለብዎ ። ስልክ ይጠቀሙ ።

• ሲመጡ እና ሲሄዱ እጅዎን ይታጠቡ ።

• ከ 1 ሜትር በላይ ወደ ታካሚው እና ወደ የጤና ሰራተኞች አይጠጉ።

• በአንድ ጊዜ ከ 2-3 ሰዎች በላይ መጎብኘት አይቻልም ።

• ጉብኝቱ በክፍሉ ውስጥ ወይም ውጭ መሆን አለበት።

• በጋራ ክፍሎቹ ውስጥ መቆየት አይቻልም ።

• ሲደርሱ ስምዎን በፕሮቶኮል እንዲጽፉ እና ጤናማ መሆንዎን እንዲያሳውቁ እንጠይቃለን ።

ምዝገባው በፈቃደኝነት ነው፣ ነገሪ ግን ምናልባት አንድ ሰው ከታመመ ማን እንደጎበኘ አጠቃላይ እይታ ይኖረናል። ካደረጉ ጥሩ ነው እና ከ 10 ቀናት በኋላ እንሰርዘዋለን ።

አንዳንድ ሰዎች ከማዘጋጃ ቤት እርዳታ የሚያገኙ ፣ በቤቶች ማህበር ውስጥ ይኖራሉ ነገሪ ግን የራሳቸው አፓርታማ አላቸው። ሆኖም ማዘጋጃ ቤቱ የግል ቤትን ማን እንደሚጎበኝ መወሰን አይችልም ። ሆኖም ግን ለጉብኝት የተሰጡ ምክሮችን እንድትከተሉ እንጠይቃለን ምክንያቱም ኮሮና አደገኛ ሊሆን የሚችል ተላላፊ በሽታ ነው ። በሚመለከታቸው ህጎች ላይ እርግጠኛ ካልሆኑ ሊጎበኙት የሚፈልጉትን ቦታ ያነጋግሩ ።

በጋራ ይህንን በሽታ እንከላከላለን!

ከሰላምታ ጋር

Skien ማዘጋጃ ቤት

SKIEN KOMMUNE

**REGIONHOVEDSTAD** VESTFOLD OG TELEMARK